# ትንቢተ ሆሴዕ (51)

## ጥናት አንድ ሆሴዕ 1፡1-2፡1

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ሃጥያታችንን ምንም እንዳልሆነና አንዳችም ችግር እንደማይፈጥር አድርጎ አይዟችሁ በማለት እንደማያልፈን የታወቀ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ሃጥያትን ባደረግንና አምላካችንን ባሳዘን ቁጥር እግዚአብሄር በቁጣው ተነስቶ ሕዝቡን ለዘለዓለም የሚጥል አምላክ እንዳልሆነ ለማስገንዘብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ሊሰፈርና ሊቆጠር እንደማይችል የባህር አሸዋ ይሆናሉ፤ ሕዝቤ አይደላችሁም በተባሉበት ቦታ የህያው አምላክ ልጆች ተብለው ይጠራሉ።" ሆሴ 1፡10

1. ሆሴዕ 1፡1-2፡1 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ስንመለከት ትንቢቱን ስለ ተናገረው ሰው ማንነትና አገልግሎት አስመልክቶ የምታያቸውን ማናቸውንም ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር። ይህንኑ ቁጥር በትኩረት ስናጤነው፤ ትንቢቱን ያመጣው ነብዩ ሆሴዕ ሲሆን፤ እርሱ የተናገረውን መልዕክት እንደማን ንግግር ወይም ቃል አድርጎ ነው የሚያቀርበው?
2. ቁ2 ላይ ያለውን ሃሳብ ስትመለከት፤ እግዚአብሄር ሆሴዕ የትንቢት አገልግሎቱን እንዲጀምር ለመላክ በተነሳበት ወቅት የነበረው የአገሪቱ ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበረ ተናገር። በዚህ ቁጥር ላይ ነብዩ ሆሴዕ የተቀበለው ተልዕኮ ለሌሎች አብዛኛውን በእግዚአብሄር ሥም ለመናገር ከሚላኩት ነብያት ልዩ የሚያደርገው ምን ነገር ትመለከታለህ? ሆሴዕ ይህንን ተልዕኮ ከእግዚአብሄር ሲቀበልና ሲወጣ ሁሉ ነገር የገባውና ጥያቄ በአዕምሮው ሳይፈጥርበት የቀረ ይመስልሃል ወይ? አንተስ በቃሉ ውስጥ እንድታደርግ የታዘዝከው ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ያልገባህን ነገር ለመታዘዝ ምን ያህል ፈቃደኛ ነህ?
3. ቁ3-4 ላይ ስናነብ ነብዩ ሆሴዕ እግዚአብሄር ባዘዘው መሰረት ትዕዛዙን መፈጸም እንደጀመረ እንመለከታለን፤ በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? በቁ2 ላይ እግዚአብሄር ለሆሴዕ መናገር በጀመረበት ጊዜና በቁ4 ላይ ደግሞ ተገልጦ ለሆሴዕ ተጨማሪ ትዕዛዝ በሰጠበት ጊዜ መካከል የነበረው የጊዜ ልዩነት ቢያንስ ምን ያህል ይሆናል?
4. ቁ4-5 ላይ ስናነብ ከነብዩ ሆሴዕና ከአመንዝራይቱ ጎሜር የተወለደው የልጃቸው ስሙ ማን እንደተባለና፤ ለዚህ ወንድ ልጅ ስሙን ያወጣለት ማን እንደነበረ ተናገር። ቁ5 ላይ ስንመለከት "በዚህ ቀን" በማለት የተነገረው አነጋገር የትኛውን ቀን የሚጠቁመን ሃሳብ ነው?
5. በጠቅላላው በምዕራፍ አንድ ውስጥ ስንመለከት እያንዳንዳቸው የሆሴዕና የጎሜር ልጆች እግዚአብሄር ስም ሲሰጣቸው የሚፈልገውን ነገር ለመግለጽ ትርጉም አያይዞ እንደነበር እናነባለን። በዚህ በቁ6-7 ላይ ለሆሴዕና ለጎሜር የተወለደችላቸውን ሴት ልጅ እግዚአብሄር ስምን ሲያወጣላት ስሟን ከምን ሁኔታ ጋራ በማያያዝ ነበረ ያወጣላት? በዚህን ወቅት የእስራኤል ሁኔታ በእግዚአብሄር ፊት ይህንን በመሰለበት ወቅት፤ የይሁዳን ሁኔታ ከእስራኤል ጋራ ሲነጻጸር ምን ይመስል ነበረ? ይህንን ማለት ለምን እንደቻልክ አስረዳ።
6. ሆሴዕና ጎሜር ሶስተኛ "ሎሃሚ" የተባለ ልጅ በቁ8-9 ላይ ያገኛሉ። እነዚህ ሁለት ባልና ሚስቶች ከወለዷቸው ልጆች መሃል መልካም ዜና ያለበት ነገር ይዞ የመጣው የትኛው ልጅ ነው ትላለህ? በቁ9 ላይ "እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም፤ እኔም አምላካችሁ አይደላችሁምና።" በማለት ሲናገር፤ በዘጸ 22፡31 ላይ የገባውን የተስፋ ቃል አጠፈ ማለት ነው ወይስ ደግሞ ሌላ ሊናገር የፈለገው ነገር ያለ ይመስልሃል?
7. የእሥራኤል ልጆች በዚህ በነበሩበት ሁኔታ ውስጥ እያሉ እንኳን እግዚአብሄር የሚያይላቸው ፍጻሜ ምን እንደሚመስል ነው በቁ10-11 ውስጥ የምንመለከተው? አንተስ በህይወትህ ለእግዚአብሄር የማትመች በሆንክባቸው ጊዜያትና ከእርሱ ጋራ የነበረህን ግንኙነት በተበላሸብህ ወቅት ላይ፤ እግዚአብሄር ተስፋህን ያደሰበት ወቅት አለ ወይ? እግዚአብሄር ሃጥያታችንን ምንም እንዳልሆነ አይዟችሁ ምንም አይደለም ብሎ እንደማያልፍ፤ ነገር ግን ደግሞ ተቆጥቶ ለዘለዓለም ሕዝቡን የሚጥል አምላክ እንደሆነ መረዳት ያስፈልገናል።

# ጥናት ሁለት ሆሴዕ 2፡2-23

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ ሊኖረን የሚገባንን ግንኙነት አበላሽተን እንደ ፈቃዳችን የተመላለስንበትን ህይወት ሁሉ ከእኛ በማራቅ መልሶ ውበት ያለው ግኙኙነት ሲያድስልን ስናይ፤ የዘልማድ ዝማሬአችንን ጥለን ልክ አዲስ ዳግም እንደተወለደ ሰው ዝማሬአችን ፍንጥዝያ የሞላው ሊሆን እንደሚገባው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በዚያም የወይን ተክሏን እመልስላታለሁ፤ የአኮርንም ሸለቆ የተስፋ በር እንዲሆናት አደርጋለሁ፤ በዚያም ከግብጽ እንደ ወጣችበት ቀን እንደ ልጅነቷም ጊዜ ትዘምራለች።" ሆሴ 2፡15

1. ሆሴዕ 2፡2-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ 2 ላይ እግዚአብሄር ለእስራኤል ልጆች ምን እንዲያደርጉ ነው ሲያዛቸው የምንመለከተው? ድርጊቷ በሌሎች በኩል ተነግሯት ሰምታ ከሃጥያቷ የማትመለስ ሆኖ ከተገኘች በቁ3-4 በተናገረው መሰረት እግዚአብሄር ሊያደርግባት ስላለው ነገር የተናገራቸውን ሃሳቦች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር።
2. በቁ5 ላይ አመንዝራዋ እስራኤል እውነተኛ ባልዋ ከነበረው ከእግዚአብሄር በመራቅ ውሽሞችዋን መከተል እንደቀጠለች ይነግረናል። ውሽሞችዋን በመከተል ከእነርሱ ልታገኝ የምትጠብቃቸውን ጸሐፊው የዘረዘራቸውን ቢያንስ አምስት ነገሮች ተናገር። እስራኤል እግዚአብሄርን በመተው ወደሌሎች የሚያስሮጧት እነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች ከእግዚአብሄር ዘንድ ሊገኙ የማይችሉ ሆነው ነው ወይስ ለምን ይመስልሃል ወደ ውጭ መሄድ ያስፈለጋት? ከዓለም የሚገኘውን ነገር ለማሳደድ ስትል ለእግዚአብሄር ያለህን ታማኝነት ጥለህ ዓለም የምትሰጠውን ቁሳቁስ ለመልቀም ፊትህን ከእርሱ የመለስንባቸውን ቀናት ታስታውሳለህ ወይ?
3. ቁ6-7 ላይ እግዚአብሄር የእስራኤልን መንገድ በእሾህ እንደሚዘጋና፣ መውጫ መንገድም እንዳታገኝ ዙሪያዋን በግንብ እንደሚያጥር ይናገራል፤ ይህንን በማድረጉ እግዚአብሄር ሊያስገኝ የፈለገው በተለይም በቁ7 ላይ የተነገረን ውጤት ምንድነው? በቁ 8 ላይ ስናነብ፤ እስራኤል ከአመንዝራነት ሌላ የነበረባት አንድ ችግር እንደነበረ ጸሐፊው ይጠቁመናል፤ ይህ ሌላው የእስራኤል ችግር ምን ነበረ?
4. በእጇ የነበረው እህሉ፣ ዘይቱ፣ የወይን ጠጁ፣ ብርና ወርቁ ሁሉ ከእግዚአብሄር እጅ የመጣ ነገር መሆኑን ለማሳወቅ ከነበረው ፍላጎት የተነሳ በቁ9-11 ላይ ስታነብ፤ ሊያደርግ ያሰባቸውና ሊወስዳቸው ያሉት እርምጃዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እግዚአብሄርን ትታ ከሌሎች ጋራ በምታደርገው ግንኙነት እግዚአብሄር አለመደሰቱና እነዚህን ሁሉ ነገሮች ሊያደርግባት መነሳቱ፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ እግዚአብሄር ባህርይ ከሚናገራቸው ነገሮች መሃል የትኛውን ያስታውስሃል?
5. እግዚአብሄርን ለማምለክና ለማገልገል ከግብጽ ባርነት ያወጣትን አምላክ ትታ የበዓል አማልክትን እንዳመለከችና እንዳጠነችላቸው ቁ13 ያሳየናል፤ ይህንን ድርጊት በማድረጓ ምክንያት ከእግዚአብሄር ስለመጣባት ነገር ቁጥሩ ምን የሚነግረን ነገር አለ? ይሆችን የሚወዳትንና ሚስቴ ብሎ እየጠራት ለምንድነው እንደገና ደግሞ እንደሚቀጣት የሚናገረው? በአንተስ ህይወት የእግዚአብሄር ተግሳጽ ወይም ቅጣት ሲመጣብህ እንደማይወድህ ነው ወይስ እንደሚወድህ የሚያረጋግጥልህ?
6. በቁ13 ላይ የምናነበው እግዚአብሄር ቅጣትን ከቀጣ በኋላ የተከተሉት በቁ14-15 ላይ የምናነባቸው "አባብላታለሁ"፣ "እወስዳታለሁ"፣ "አነጋግራታለሁ"፣ "እመልሳታለሁ"፣ "አደርጋለሁ" የሚሉት አነጋገሮች በሙሉ ትኩረታቸው በማን እንደሆነ ነው የምታየው? እግዚአብሄር በእስራኤል ህይወት በቁ14-15 ላይ የምናያቸውን በሚፈጽምበት ጊዜ፤ የእስራኤል ምላሽ ምንድነው ይለናል ክፍሉ? እግዚአብሄር ላጠፋኸው ጥፋት ምህረት አድርጎ ሲመልስና ሲቀበልህ የአንተ ምላሽ ምን ይሆን?
7. እግዚአብሄርና እስራኤል ያላቸውን ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱሳችን በተለያዩ መንገዶች እንደሚገልጽ እናውቃለን፤ በቁ16-20 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት፣ የእግዚአብሄርንና የእስራኤልን ግንኙነት ለመናገር በተደጋጋሚ የተጠቀመበትን አንድ ሃሳብ ተናገር። ቁ21 እና ቁ22ትን ስናነብ፤ ምድር ፍሬዋን እንድትሰጥ ካስፈለገ፤ መከናወን የሚኖርባቸው ወይም በቅደም ተከተል መሆን የሚኖርባቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? እግዚአብሄር ትዕዛዝን ለሰማይ ካልሰጠ ሰማይም ሆነ ምድር አንዳች ማድረግ ስለማይችሉ፤ የነገሮች ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሄር እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው።
8. "እንደ ልጅነቷም ጊዜ ትዘምራለች" የሚለውን በቁ15 ላይ ያለውን ሃሳብ ስንመለከት፤ እንደ ልጅነት ጊዜ መዘመር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ነው የምትረዳው? በልጅነትህ ወይም ገና ጌታ በተቀበልክበት ወቅት የነበረህ የዝማሬ ዓይነት አሁን ካለህ የዝማሬ ህይወት የተለየ ነበረ ወይ?
እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ ሊኖረን የሚገባንን ግንኙነት አበላሽተን እንደ ፈቃዳችን የተመላለስንበትን ህይወት ከእኛ በማራቅ መልሶ ውበት ያለው ግኙኙነት ሲያድስልን ስናይ፤ የዘልማድ ዝማሬአችንን ሳይሆን ልክ አዲስ ዳግም እንደተወለደ ሰው ዝማሬአችን ፍንጥዝያ የሞላው ሊሆን ይገባል።

# <u>ጥናት ሶስት ሆሴዕ 3፡1-4፡19</u>

የጥናት ዓላማ፡- ከእስራኤል ታማኝነት፣ ፍቅርና፣ እግዚአብሄርን ማወቅ በጠፋ ጊዜ፤ ርግማን፣ ውሸት፣ መግደል፣ ሥርቆት፣ ማመንዘርና የቃል ኪዳን ማፍረስ ምድሪቱን እንዳጥለቀለቃት ሁሉ፤ ከእኛ ህይወትም እነዚህን ሶስት ነገሮች ማስወጣት ስንጀምር፤ ከላይ በተዘረዘሩት ነገሮች ፈጥነው ስፍራውን መውሰድ እንደሚጀምሩ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ታማኝነት የለም፣ ፍቅርም የለም፣ እግዚአብሄርንም ማወቅ በምድሪቱ የለም፤ በዚያ ያለው ርግማን፣ መዋሸት፣ መግደል፣ መስረቅ፣ ማመንዘር ብቻ ነው፤ ቃል ኪዳንን ሁሉ ያፈርሳሉ፤ ደም ማፍሰስና ግድያ ይበዛል።" ሆሴ 4፡1-2

1. ሆሴዕ 3፡1-4-19 በአንድነት ይነበብ፡፡ በ3፡1 ላይ ሆሴዕ ከእግዚአብሄር ትዕዛዝን ሲቀበል እንመለከታለን፤ ይህ ነብዩ ሆሴዕ እንዲያደርግ ከእግዚአብሄር የተቀበለው ትዕዛዝ ምን የሚል ነበረ? አመንዝራነቷን ለማካሄድና ከሌሎቹ ወዳጆችዋ ጋራ ለመማገጥ ከእርሱ የተለየችውን ሚስቱን እንደገና እንዲወዳትና ወደራሱ እንዲመልሳት እግዚአብሄር ለሆሴዕ ትዕዛዝ የሰጠበት ዋነኛው ምክንያቱ ምን ነበረ?
2. በቁ3 ላይ ስንመለከት ሆሴዕ የገዛ ሚስቱ የሆነችውን ጎሜርን እግዚአብሄር መልሶ እንዲወዳት ሲነግረው እርሱም በመታዘዝ ክፍያ በመክፈል ሚስቱን እንደገዛ እንመለከታለን፤ የገዛ ሚስቱ ሆና እያለች ሆሴዕ ሚስቱን ከመውሰድ ይልክ ክፍያ መክፈል ያስፈለገው ምክንያት ለምን ይሆናል ብለህ ታምናለህ? ቁ4-5 ውስጥ ስናነብ፤ የእስራኤል ሕዝብ ሊያልፍ ያለባቸውን ሁለት የህይወት ደረጃዎች ይጠቁመናል፤ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተነገሩን ይህ ህዝብ ሊያልፍባቸው ያሉት እነዚህ ሁለት የሕይወት ደረጃዎች ምንና ምንድናቸው?
3. በቁ 2 ላይ በተዘረዘሩት በአገሪቱ ላይ በተካሄዱት ርካሽ ድርጊቶችና ሰዎቹ ባደረጉት ጦስ ማለትም፤ በእርግማኑ፣ በውሸቱ፣ በግድያው በሥርቆቱ፣ በምንዝርናው፣ በቃል ኪዳን ማፍረሱ፣ በደም ማፍሰሱና በግድያው መብዛት የተነሳ በቁ3 ላይ የምናያቸው ሶስቱ ጉዳተኞች እነማን እንደሆኑ ተናገር። ቁ3 በነገሩ የተጎዱትን ሲያሳየን፤ ቁ4ትን እና 5ትን ስንመለከት ደግሞ ሶስቱን ለዚህ በአገሪቱ ላይ ለሆነው ነገር ተጠያዊ የሆኑትን ሶስቱ እነማን እንደሆኑ ይጠቁመናል፤ ለሁኔታው ተጠያቂዎቹ የተባሉት ሶስቱ እነማን ናቸው?
4. በእስራኤል ውስጥ ለሆነው የህይወት ማሽቆልቆልና የህዝብ መረን መውጣት የተለያዩ ሁኔታዎችን መጠቆም ቢቻልም እንኳን፤ እግዚአብሄር ዋነኛ ችግር አድርጎ የተመለከተውን በቁ6 ላይ በግልጽ ይነግራቸዋል፤ ይህ በቁ 6 ላይ ለችግራቸው ሁሉ ዋነኛ አድርጎ የተናገረው ነገር ምንድነው? በዚህ በህዝቡ እውቀት ማጣት ካህናቱ የነበራቸው አስተዋጽዖ ምን ነበረ?
5. በቁ7-8 ላይ በተለይም ቁ7ት ላይ እግዚአብሄር "ካህናት በበዙ ቁጥር፤ በእኔ ላይ የሚያደርጉት ሃጥያት በዝቷል" ብሎ ሲናገር፤ ብዙ ካህናት መኖራቸው ህዝቡን የህዝቡን ሃጥያት ያበዛዋል ማለት ነው ወይስ ካልሆነ ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? በቁ8 ላይ "የህዝቤ ሃጥያት ለመብል ሆኖላቸዋል፣ ርኩሰታቸውንም እጅግ ወደዱ።" በማለት የሚለውን አነጋገር እንዴት ትርዳዋለህ? በቤተ ክርስትያንም ውስጥ በጣም ብዙ አገልጋዮች አሉ ማለት ሁልጊዜ የእግዚአብሄር ህዝብ እግዚአብሄርን ማወቅ እየተማረ ነው ማለት ላይሆን እንደሚችል ማሰብ ይጠቅማል።
6. ቁ10-13ትን ስናነብ፤ የእግዚአብሄር ቤት አገልጋዮች የሆኑት ካህናት እየፈጸሟቸው ያሉት የተዘረዘሩት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ የሚታዩህን ሁሉ ተናገር። በእነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ ካህናቱ እየተለማመዷቸው ላሉት አጸያፊ ምግባሮቻቸው፤ በቁ13-14 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ፍርዱን በእነርሱ ላይ የሚያመጣባቸውን መንገዶች ይናገራል፤ እነዚህ እግዚአብሄር ያሰባቸው ፍርዶች ምን ምንድናቸው?
7. በምዕራፍ አራት መጨረሻ በተለይም ከ15-19 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ለይሁዳ የሚሆን የማስጠንቀቂያ ቃል ሲናገር እንመለከተዋለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ይሁዳ እስራኤልን እንዳይመስል የሚያስጠነቅቃቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? ለምንድነው ይላል እግዚአብሄር ይሁዳ የእስራኤልን ፈለግ እንዳይከተል የሚመክርበት ምክንያት? ቁ16 ላይ እንደልባቸው በሃጥያት የሚመላለሱና እልከኝነት የማይለቃቸው ሰዎች፤ በመዝ 23፡2 ላይ እንዳለው አይነት ዝማሬን መዘመር ይችላሉ ወይ?
8. ቁ4፡1-2ትን መለስ ብለን በምናነብበት ጊዜ እግዚአብሄር በእስራኤል ምድር በሚኖሩት ሰዎች ላይ ያለውን ክስ ያሰማል፤ አስቀድሞ እግዚአብሄር በምድሪቱ ላይ እንደሌሉ በመንገር ህዝቡን የሚከስባቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በምድሪቱ የሌሉትን ነገሮች ከተናገረ በኋላ፤ ምድሪቱን የሞሉትን ነገሮች ሲናገር የዘረዘራቸውን ሁሉንም አንድ በአንድ ተናገር። ርግማን፣ ውሸት፣ ግድያ፣ ስርቆት፣ ምንዝርና፣ ቃል ኪዳን ማፍረስና የመሳሰሉት እግዚአብሄር የሚያዝንባቸው ነገሮች ህይወታችንን እንዳይወሩት ካስፈለገ አኗኗራችን በታማኝነት፣ በፍቅርና፣ እግዚአብሄርን በማወቅ የተሞላ ሊሆን ያስፈልጋል።

# <u>ጥናት አራት ሆሴዕ 5፡1-6፡11</u>

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር በህይወታችን እንዲመጣ የፈቀደውን ነገር ወደ ማንም አዋቂ ወይም ብርቱ ሰው ብንሄድ መፍትሄን ሊሰጠን ስለማይችል፤ ብቸኛ የሆነው መፍትሄ፤ ትዕቢታችንንን ከእኛ አስወግደንና ራሳችንን ዝቅ አድርገን ከአምላካችን ጋራ ነገራችንን ማስተካከል መሆኑን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ኤፍሬም ህመሙን፣ ይሁዳም ቁስሉን ባየ ጊዜ ኤፍሬም ወደ አሶር ሄደ፤ ርዳታ ለመጠየቅ ወደ ታላቁ ንጉሥ መልዕክተኛ ላከ፤ እርሱ ግን ሊያድናችሁ፤ ቁስላችሁንም ሊፈውስ አይችልም።" ሆሴ 5፡13

1. ሆሴዕ 5፡1-6፡11 በአንድነት ይነበብ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን አንዳንድ ጊዜ ኤፍሬም የሚለውን ሃሳብ ለእስራኤል ባጠቃላይ መጠሪያ አድርጎ ሲጠቀምበት ይታያል፤ ሆኖም በዚህ ክፍል ግን ለሁለቱም ለእያንዳንዳቸው መልዕክት አለው። ሆሴ 5፡3 ላይ ኤፍሬምን አስመልክቶ እግዚአብሄር የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? ይኸው ቁጥር እስራኤልን አስመልክቶ የሚናገራቸውስ ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? ከዚህ ክፍል እንደምንመለከተው እግዚአብሄር ስለ ኤፍሬምና እስራኤል ያለውን እውቀት መጠን ስትመለከት፤ ስለራስህ ምን የሚያስተምርህ ነገር አለ?
2. በቁ5-7 ላይ ደግሞ ስንመለከት እግዚአብሄር በሶስቱም ማለትም፤ በኤፍሬም፣ በእስራኤልና፣ በይሁዳ ላይ አተኩሮ ሲናገር እናየዋለን። በቁ5 ላይ ሶስቱም በሃጥያታቸው እንደተሰናከሉ ተነግሮላቸው፤ በቁ6 ላይ ሊያደርጉ ሲሞክሩ የሚታየው ነገር ምንድነው? በቁ6 ላይ ኤፍሬም፣ እስራኤልና፣ ይሁዳ ላይ ሲሆን የምናየው ነገር፤ በኢሳ 55፡6 ላይ ከሰፈረው እውነት ጋራ የሚመሳሰልበት ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
3. ቁ12-15ት ላይ ያሉትን ቁጥሮች ስናነብ፤ እግዚአብሄር ኤፍሬምንና ይሁዳን ለመቅጣት ያደረገውን ነገር ሲናገር፤ ለእነዚህ ለሁለቱ እንደምን ሆንኩላቸው በማለት ነው የሚናገረው? እግዚአብሄር ለእነዚህ ሁለት ነገዶች ራሱ እንደ አንበሳና፣ እንደ ደቦል አንበሳ እንደሚሆንባቸው ሲያስታውቅ ቁ14 አነጋገር መሰረት እግዚአብሄር ይህንን ማለቱ ትርጉሙ ምን ማለት ነው? እግዚአብሄር በኤፍሬምና በይሁዳ ላይ ይህንን ክፉ ነገር ሊያደርግ የቆረጠው እስከ መቼ ድረስ ነው?
4. ነብዩ ሆሴዕ በ6፡1-3 ላይ ራሱን ከህዝቡ እንደ አንዱ በመቁጠር የሚናገረውን ሃሳብ እንመለከታለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ነብዩ ሆሴዕ ምን በማለት ነው ህዝቡን ሲያደፋፍር የሚታየው? ሆሴዕ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ለህዝቡ የሚያቀርብላቸው ከልብ የመነጨ የፍቅር ምክር በምን መንገድ ነው በ5፡13 ላይ ከተመለከትነው እነርሱ ካሰቡትና ካደረጉት ድርጊት የሚለየው? እግዚአብሄር ይህንን ሆሴዕ የተናገረውን ነገር እንደሚያደርገው ምን ያህል እርግጠኛ ነበረ ትላለህ?
5. ቁ4 ላይ ስንመለከት የእግዚአብሄር ህዝቦች ለአምላካቸው ምንም ዓይነት ፍቅር እንደሌላቸው ነው የሚናገረው ወይስ በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄር ስለህዝቡ የሚያዝንበት አንድ እውነት ምንድነው ትላለህ? እግዚአብሄር አምላክ ይህን ሁኔታ ለመቀየር ያደረጋቸውንም ጥረቶች በቁ5 ላይ ይዘረዝራል፤ እነዚህ እግዚአብሄር የህዝቡን ፍቅር በቋሚነት ለማግኘት የወሰዳቸው እርምጃዎች ምን ምንድናቸው?
6. በ5፡6 ላይ እንደተመለከትነው ህዝቡ የሚያደርገውን ሁሉ ርኩሰት እያደረገ ለእግዚአብሄር መስዋዕትንና የሚቃጠለውን መስዋዕት ማቅረቡን እንዳልተወ እናውቃለን፤ ሆኖም እግዚአብሄር በ6፡6 ላይ ህዝቡ እንዲረዳውና እንዲገባው የፈለገው መሰረታዊ እውነት ምንድነው ትላለህ? ይህንን በዚህ ቁጥር ላይ የምንመለከተውን አነጋገር ስናይ፤ እግዚአብሄር መስዋዕትና የሚቃጠል መስዋዕት እንዲቀርብለት አይፈልግም ማለት ነው ወይስ ካልሆነ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ።
7. ቁ12-13ትን ስናይ፤ ኤፍሬምና ይሁዳ እግዚአብሄር ካመጣባቸው በሽታ ወይም ቅጣት ለመገላገል የወሰዱት እርምጃ ምን ያህል መፍትሄ ሆኖላቸዋል ብለህ ታምናለህ? አንተስ በህይወትህ ከገጠመህ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት መፍትሄ አድርገህ የምትሄደው ወደማን ነው? እግዚአብሄር በህይወታችን እንዲመጣ የፈቀደውን ነገር ወደ ማንም አዋቂ ወይም ብርቱ ሰው ብንሄድ መፍትሄን ሊሰጠን ስለማይችል ቸኛ መፍትሄው፤ ራሳችንን ዝቅ አድርገን ከእርሱ ጋራ ነገራችንን ማስተካከል መሆኑን ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት አምስት ሆሴዕ 7፡1-8፡14

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ቃሉን የሰጠን ምክንያት የእለት ተእለት ህይወታችንን እንድንመራበት እንጂ፣ በቤታችን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለ ሰዎች እንዲያውቁ ወይም ለክርስትናችን ማረጋገጫ እንዲሆነን እንዳልሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በህጌ ውስጥ ያለውን ብዙውን ነገር ጻፍሁላቸው፣ እነርሱ ግን እንደ እንግዳ ነገር ቆጠሩት።" ሆሴ 8፡12

1. ሆሴዕ 7፡1-4፡14 በአንድነት ይነበብ፡፡ በ7፡1-2 ላይ እግዚአብሄር ለእስራኤል ሃጥያት ይቅርታና ፈውስ ሲሰጥ ተመልሰው ወደሃጥያታቸው ለመመለስ ከመቸኮላቸውና ሐጥያት ከመስራታቸው ባሻገር አንድ የሚዘነጉት ነገር እንዳለ በቁ2 ላይ ይነግራቸዋል፣ ይህ የእስራኤል ህዝብ የሚዘነጋው ተብሎ የተጠቀሰው ነገር ምንድነው፡፡ ሃጥያተኛነቱን ከልቡ አምኖና ተናዞ ለሚተዋት ሰው እግዚአብሄር በኤር 31፡34 ላይ የገባለት የተስፋ ቃል ከዚህ በምን የተለየ ሆኖ ታየዋለህ?
2. በቁ4-7 ባለው ክፍል ውስጥ የእነዚህን ሰዎች ማንነትና ምንነት ለመግለጽ እግዚአብሄር በነብዩ ሆሴህ አማካኝነት ሲጠቀምበት የምንመለከተው አንድ አይነት አባባል ቢያንስ አራት ጊዜ በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሶ የሚገኝ ቃል እናያለን፣ ይህ የተጠቀመበት ቃል ምን የሚል ነው? ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በሮሜ 12፡11 ላይ ውስጣቸው በመንፈስ የሚቃጠል እንዲሆን እንዲሆን ሲነግራቸው እንመለከታለን፣ ይህ ጳውሎስ የሚናገረው መቃጠልና፣ ሆሴ 7፡6 ላይ የምናነበው ዓይነት መቃጠል ልዩነቱ ምንድነው?
3. በቁ8-10 ላይ ስናነብ በኤፍሬም ህይወት ውስጥ እየሆኑ እንዳሉ የምንመለከታቸው ቢያንስ ሶስት ነገሮች አሉ፣ እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑና ለእነዚህ ነገሮች ደግሞ የኤፍሬም ምላሽ ምን እንደሆነ ተናገር። ቁ8 "ኤፍሬም ከአህዛብ ጋራ ተደባለቀ፣ ኤፍሬም ያልተገላበጠ ቂጣ ነው" ይላል። ኤፍሬም ከአህዛብ ጋራ መደባለቁና፣ ኤፍሬም ያልተገላበጠ ቂጣ መሆኑ የሚገናኙበት ምን መንገድ ይታይሃል?
4. ኤፍሬም በቀላሉ እንደምትታለል አዕምሮ እንደሌላት ርግብ እንደሆነ በቁ11 ላይ ይነግረናል። ከቁ11-16 ባለው ክፍል ውስጥ ስንመለከት ኤፍሬም አዕምሮ እንደሌለው ሆኖ የሚታይባቸው ምን ሁኔታዎችን ትገነዘባለህ? በቁ16 ላይ እግዚአብሄር "ወደ ከንቱ ነገር ተመለሱ፣ ዒላማውን እንደሳተ ቀስት ናቸው" በማለት ስለ ኤፍሬም ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ስለ አንተስ በእግዚአብሄር ቢናገር ዒላማህን እንደሳትክ ነው ወይስ ዒላማህን እንደምትመታ ቀስት ይናገር ይመስልሃል?
5. ሆሴ 8፡1-3 ትን ስንመለከት፣ በተለይም ቁ1 ከሚናገረው አንጻር የእግዚአብሄር ህዝቦች ያደረጓቸውና እየተወቀሱ ያሉባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ከእነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ሳንወጣ፣ በቁ2 ላይ ህዝቡ በሚናገሩት አነጋገር ስትመለከትና፣ በቁ3 ላይ ደግሞ የሚያደርጉትን ድርጊት ስትመለከት ተቃራኒ ሆኖ የሚገኘው በምን መንገድ ነው? እኛም የጌታ ልጆች የሆንን ሁላችን በአንደበታችን ብቻ እግዚአብሄርን አውቃለሁ በማለት፣ በድርጊታችን ግን መልካምን ነገር የምንንቅ እንዳንሆን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል።
6. 8፡4 ላይ ስናነብ ከእግዚአብሄር ዘንድ ምክርን ሳይጠይቁና የእርሱን ፈቃድ ምን እንደሆነ ሳያውቁ የእስራኤል ህዝብ የወሰዷቸው ሁለት እርምጃዎች በዚህ ክፍል ተጠቅሰዋል፣ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህ የእግዚአብሄር ህዝብ በመባል የሚጠሩ ሰዎች ለፍተውና ጥረው ግረው የሚያገኙትን ገንዘብ የሚያወጡት በምን ላይ እንደሆነ ነው ከክፍሉ የምንረዳው?
7. 8፡5-8 ባለው ክፍል ላይ ስታነብ፣ እስራኤላውያን ከእግዚአብሄር ጋራ የነበራቸውን ግንኙነት በማበላሸታቸው ምክንያት የተነሳ በእነርሱና በምድራቸው ላይ ስለደረሱት ነገሮች የምታያቸውን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር። 8፡9-11 ላይ ስንመለከት፣ ኤፍሬም ሃጥያቱን ለማስተሰረይና ምንም የማያደርግ ህዝብ ሳይሆን፣ ነገር ግን የኤፍሬም ጥፋቱ ምን እንደሆነ ነው ከክፍሉ የምንረዳው? አንተስ ለበጎ ብለህ የጀመርከው ነገር ለህይወትህ እንቅፋት የሆነብህ ነገር አለ ወይ?
8. በምዕራፍ 8 ቁ12 ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር በኤፍሬም ላይ ያለው ቅሬታ ምን ነበረ? አንተስ በእጅህ ያለው የእግዚአብሄር ቃል ዘወትር ህይወትህን የምትመራበት መጽሐፍ ነው ወይስ እንደ እንግዳና ባዳ ነገር አንድ ጥግ አስይዘኸዋል? እግዚአብሄር ቃሉን የሰጠን የእለት እለት ህይወታችንን እንድንመራበት መጽሐፍ እንዲሆን እንጂ፣ በቤታችን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለና ክርስትናችንን ማረጋገጫ መጽሐፍ ብቻ ሊሆን አይገባም።

# ጥናት ስድስት ሆሴዕ 9፡1-10፡15

የጥናት ዓላማ፡- ከኤፍሬም ህይወት እንደምንማረው፤ ከሃጥያት ጋራ ጓደኛነታችንን በማዳበር፣ ከእግዚአብሄር ጋራ ደግሞ ከወዳጅነት ይልቅ ጠላትነት ማስተናገድ ስንመርጥ፤ በትክክለኛ ጎዳና ላይ እንዳልሆንን ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ግልጽ ሆኖ የሚታየው ነገር፤ ከእግዚአብሄር የሆነውን እውነት የሚነግሩንን ሰዎች እንደ ሞኝ፤ በቅድስና እግዚአብሄርን እየፈሩ የሚኖሩትን ቅዱሳን ደግሞ አዕምሮ እንደጎደላቸው እብዶች አድርገን የመቁጠር ባህርይ ስናዳብር እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የቅጣት ቀን መጥቷል፣ የፍርድም ቀን ቀርቧል፤ እስራኤልም ይህንን ይወቅ፣ ሃጥያታችሁ ብዙ፣ ጠላትነታችሁም ታላቅ ስለሆነ፤ ነብዩ እንደ ሞኝ፤ መንፈሳዊውም ሰው እንደ እብድ ተቆጥሯል።" ሆሴ 9፡7

1. ሆሴዕ 9፡1-10፡15 በአንድነት ይነበብ፡፡ ሆሴ 9፡1-6 ላይ ስንመለከት ሌሎች በአካባቢው ያሉት ሕዝቦች እንደሚያደርጉት ሁሉ የእግዚአብሄር ሕዝብ የተባለችው እስራኤል ደስተኛ እንዳትሆንና ሃሴት እንዳታደርግ እግዚአብሄር ሲከለክል እንመለከታለን፤ ለምንድነው እነዚህ ሰዎች ደስታና ሃሴት እንዳያደርጉ የተከለከሉት? በፊሊ. 4፡6 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በጌታ ደስ እንዲለን ደጋግሞ ይነግረናል። ጳውሎስ የሚናገረውን ሃሳብና በዚህ በሆሴ 9፡1 ላይ ያነበብነውን ሃሳብ ስንመለከት ስለአማኝ ደስታ አስመልክቶ መማር የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው?
2. ሆሴ 9፡7-9 ላይ በተለይም ደግሞ ቁ8ትን ስንመለከት፤ የእግዚአብሄር ነብያት በእግዚአብሄር ሕዝብ ላይ የነበራቸው ሚና ምን እንደ ነበረ ነው ከቁጥሩ የምንረዳው? እነዚህ ነብያት ለህዝቡ ለሚያደርጉ መልካም ነገር የእግዚአብሄር ህዝቦች ከተባሉት ሰዎች የሚገጥሟቸው ምን ዓይነት ነገሮች እንደነበሩ ተናገር።
3. ሆሴ 10-17 ሲነበብ፤ እግዚአብሄር በእርሱና በእስራኤል መሃል ቀድሞ ስለነበረው ግንኙነት ሲናገር እናገኘዋለን፤ በእግዚአብሄርና በእስራኤል መሃል የነበረውን የቀድሞ ግንኙነታቸውን ምን በማለት ነው የሚናገረው? ብዔልፌጎር ወደ ተሰኘው ሥፍራ በመጡ ጊዜ (ስለ ብዔልፌጎርና በዚያ ስለሆነው ነገር በይበልጥ ለመረዳት ዘሑልቁ ምዕራፍ 25ትን በሙሉ ማንበብ ይረዳል።) የእግዚአብሄርና የእስራኤል ግንኙነት እንደተበላሸ ይታያል። ግንኙነታቸውን ያበላሸው ነገር ምን ነበረ?
4. ሆሴ 10፡1-3 ትን ስናነብ፤ እግዚአብሄር ለእስራኤል ያደረገውን መልካም ነገርና፤ እስራኤል ደግሞ ከእግዚአብሄር የተቀበለውን በረከት በምን ላይ እንዳዋለው ቁ1 ላይ ማየት እንችላለን፡፡ በዚህ ቁጥር መሰረት እግዚአብሄር ለእስራኤል ያረገው ምን እንደነበረና እስራኤል ደግሞ ለምን እንደተጠቀመበት የተነገሩትን ሃሳቦች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር። ቁ3 ላይ "…እግዚአብሄርን አላከበርንምና፤ ንጉስ ቢኖረንስ ምን ሊያደርግልን ይችል ነበር? ይላሉ" የሚለው የእስራኤላውያን አነጋገር ምን ያህል እውነትነት አለው ትላለህ? አንተስ እግዚአብሄርን በማያከብር ሕይወት ውስጥ እየኖሩ መሪ ያለው ሕዝብ መባል ብቻ ምን ያህል እርካታ ይሰጥሃል?
5. ሆሴ 10፡4-10 ያሉት ቁጥሮች በአንድነት ይነበቡና በተለይም በቁ9 እና በቁ10 ላይ በማተኮር ስንመለከት፤ እግዚአብሄር በዚህ ክፍል ውስጥ እስራኤል በጊብዓ ላይ ሃጥያት ማድረግ እንደጀመረ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ ስለ ሃጥያታቸው የሚናገረው ነገር ምንድነው? ቁ10 ላይ "በፈለግሁ ጊዜ እቀጣቸዋለሁ" በማለት እግዚአብሄር መናገሩ እነዚህ ሰዎች ከሃጥያት ነጻ ሆነዋል ማለት ነው ወይ? ሃጥያትን ገና ከሩቁ ሳይጀመር መቅጨት እንጂ ስር እየሰደደ የሚሄድ ነገር ስለሆነ አስቀድሞ በተቻለ መጠን ከሃጥያት ጋራ የሚኖረንን መነካካት ወይም ከሃጥያት ጋራ ጨዋታ እንደማያዋጣን ልናውቅ ያስፈልጋል።
6. ሆሴ 10፡11-15 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ኤፍሬም ያደርገው ዘንድ የመከረውን ሃሳብና፤ ኤፍሬም ደግሞ በአንጻሩ ሲያደርግ የሚገኘውን ነገር ቁ12 እና ቁ13 ላይ ይነግረናል። ኤፍሬም እንዲያደርግ የተመከራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። የእግዚአብሄር ምክር ለኤፍሬም ይህ ሆኖ እያለ፤ ኤፍሬም ሲያደርግ የሚታየው ነገሮችስ ምን ምንድናቸው?
7. በሆሴ 9፡7 የምንመለከታቸው ሰዎች የእግዚአብሄርን እውነት የሚያመጣላቸውን ነብይ እንደ ሞኝና፤ ከእግዚአብሄር ጋራ በጽድቅ የሚኖረውን መንፈሳዊ ሰው እንደ እብድ እንዲቆጥሩ የሆኑበት ምክንያቱ ምንድነው? የእግዚአብሄርን እውነት የሚነገሯቸውን ሰዎች እንደ ሞኝና፤ በቅድስና እግዚአብሄርን እየፈሩ የሚኖሩትን ሰዎች ደግሞ አዕምሮ እንደጎደላቸው እብዶች እንደሆኑ የሚናገሩ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ? ሰዎች የራሳቸው ህይወት እያሽቆለቆለ የሃጥያት ጓደኞች፤ የእግዚአብሄር ግን ጠላቶች በመሆን ሲመላለሱ፤ የእግዚአብሄርን እውነት የሚነገሯቸውን ሰዎች እንደ ሞኝ፤ በቅድስና እግዚአብሄርን እየፈሩ የሚኖሩትን ደግሞ አዕምሮ እንደጎደላቸው እብዶች መቁጠር ባህርያቸው እየሆነ ይሄዳል።

# <u>ጥናት ሰባት ሆሴዕ 11፡1-12፡14</u>

የጥናት ዓላማ፡- ከኤፍሬም ህይወት በመማር፤ እግዚአብሄር ከሃጥያታችን ተመልሰን ከእርሱ ጋራ ያለንን መልካሙን የአባትና የልጅነት ግንኙነታችንን እንድናድስ ሲመክረንና ሲያስጠነቅቀን ልባችንን ከማጠጠር ይልቅ፤ ንስሃ በመግባት መመለስ እንደሚረባን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ታዲያ ንስሃ መግባትን እንቢ በማለታቸው ወደ ግብጽ አይመለሱምን? አሶርስ አይገዛቸውምን? በከተሞቻቸው ላይ ሰይፍ ይመዘዛል፣ የበሮቻቸውን መወርወሪያ ይቆርጣል፣ ስለ ክፉ እቅዳቸውም ይደመስሳቸዋል።" ሆሴ 11፡5-6

1. ሆሴዕ 11፡1-12፡14 በአንድነት ይነበብ። ሆሴ 11፡1ድን በምናነብበት ጊዜ የእግዚአብሄርና የእስራኤል ወዳጅነት የጀመረበት ወቅት መቼ እንደነበረ እንመለከታለን፤ ይህ ግንኙነት የጀመረው መቼ ነበረ ነው የሚለን? በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄር ስለ እስራኤል የተናገረውን "ልጄን ከግብጽ ጠራሁት" የሚለውን ሃሳብ በመውሰድ፤ ማቴዎስ ትርጉሙ በእስራኤል ላይ ብቻ የሚቀር እንዳልሆነና የትንቢትነት ቃልም እንዳለበት በመረዳት በማቴ 2፡14-15 ላይ ለምን ዓይነት ሃሳብ ሲጠቀምበት ወይም ሲያውለው ነው የምትመለከተው?
2. በቁ2-4 ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር ከእስራኤል ጋራ የነበረውን የፍቅር ግንኙነት በምን መንገድ ሲኮተኩትና መደረግ ያለበትን ሁሉ ሲያደርግ እንደነበረ ይናገራል። ለእስራኤልና ለእግዚአብሄር ግንኙነት እግዚአብሄር አደረጓቸው የሚላቸውን ነገሮች ከእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በማውጣት ምን ምን እንደሆኑ በመናገር፤ በአንጻሩ ደግሞ ከዚያው ጋራ በማያያዝ እስራኤል እግዚአብሄር ላደረጋቸው ሙከራዎች ሁሉ ይሰጡ የነበሩት ምላሽ ምን እንደነበረ አብረህ ተናገር።
3. እስራኤል ከአምላኩ ጋራ የነበረውን የፍቅር ግንኙነት እንደሚገባ ለመያዝ አሻፈረኝ ማለቱ ያስከፈለው ዋጋ እንደነበረ ቁ5-7 ያለው ክፍል ይነግረናል፤ ለዚህ እንቢተኛነቱ እግዚአብሄር እስራኤልን እንዲከፍል ያደረጋቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? እግዚአብሄር ለሚናገርህና ላስጠነቀቀህ ነገር እንቢተኛ በመሆን እንቢተኛነትህ ዋጋ አስከፍሎህ ያውቃል ወይ?
4. ሆሴ 11፡8-11 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር በላይኛቹ ቁጥሮች ውስጥ ይናገር የነበረውን ዓይነት ንግግር አይደለም ሲናገር የምንሰማው፤ በተለይም በቁ8-9 ላይ የምንመለከተው የእግዚአብሄርን የትኛውን ባህርዩን አጉልቶ የሚያሳየን? በቁ10-11 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሄር ለእስራኤል ልጆች ለወደፊታቸው የሚያይላቸውን ነገር ምን እንደሆነ አስፍሮልናል፤ እግዚአብሄር ከቁጣው ተመልሶ በርህራሄው እስራኤልን በመመልከት በሕዝቦቹ ህይወት ውስጥ ለወደፊት ሊያደርግ ያቀደው ነገር ምንድነው?
5. የነብዩ ሆሴዕ አገልግሎት ቢያንስ አርባ ዓመታት ያካተተና በእነዚህም ዓመታት መሃል ብዙ የተከናወኑ ነገሮች እንደሚኖሩም አያጠራጥርም። በ4፡15 ላይ እግዚአብሄር ለእስራኤል በሚያስጠነቅቀው ማስጠንቀቂያና፤ በሆሴ 11፡12 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ያስጠነቀቀውና ተፈጽሞ የምታይው አንድ ነገር ምንድነው? ከሆሴ 11፡12 ጀምሮ እስከ 12፡1 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሄር የኤፍሬምን ድርጊት አስመልክቶ እየተናገረ ያለባቸውን ቢያንስ አምስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
6. ሆሴ 12፡2-5 ባሉት ቁጥሮች ላይ ስናነብ እግዚአብሄር በያዕቆብ ላይ ሊፈርድ እንዳለ እንመለከታለን። በተለይም ቁ2ትን ስንመለከት ስለ እግዚአብሄር ፍርድ ወይም ቅጣት የሚያስተምረን አንድ እውነት ምንድነው? ይህ ክፍል ያዕቆብ በተለያየ የህይወት ደረጃ ውስጥ ሆኖ ያደረጋቸውን ሁለት ዓይነት ትግሎች ይነግረናል፤ እነዚህ ሁለት ትግሎች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
7. ሆሴ 12፡6-14 ላይ ባሉት ክፍሎች ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሄር ከህዝቡ የሚጠብቀው ነገር ምን እንደሆነና የሕዝቡ ድርጊት ደግሞ ምን እንደሆነ እናያለን። በተለይ ቁ6 ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር ከህዝቡ የሚጠብቃቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? በቁ7-8 ውስጥ ስናነብ የምንመለከታቸው የእግዚአብሄር ሕዝቦች የሚለማመዷቸው የሐጥያት ዓይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
8. ወደ ሆሴ 11፡5 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት እስራኤል ወደዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ እንዲገባ የዳረገው ዋነኛ ነገር ምን እንደሆነ ነው የምንመለከተው? አንተስ እግዚአብሄር ሲናገርህና ተመልሰህ በፍቅሩ ውስጥ እንድትኖር ሲያስጠነቅቅህ ልብህን በማደንደን በእንቢተኛነት ታስቸግረዋለህ ወይ? እግዚአብሄር ከከፉ ስራችን ተመልሰን ከእርሱ ጋራ ያለንን መልካሙን የልጅነት ግንኙነት እንድናድስ ሲመክረንና ሲያስጠነቅቀን በንስሃ ልብ ቶሎ መመለስ ይኖርብናል።

# ጥናት ስምንት ሆሴዕ 13፡1-14፡9

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር መንገድ ወይም ደግሞ የተሰጠን የእግዚአብሄር ቃል እየታዘዝን የምንሄድበት ወይም የምንመላለስበት ነገር እንጂ፤ እንዲሁ በከንቱ የምንሰማው፣ ወይም ለሌሎች የምናሰማው ወይም ደግሞ ሆሴ 14፡9 እንደሚለው፤ እንደ አመጸኞች የምንሰናከልበት ነገር እንዳይሆን መጠንቀቅ እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ጥበበኛ የሆነ እነዚህን ነገሮች ያስተውላል፤ አስተዋይም እነዚህን ነገሮች ይረዳል። የእግዚአብሄር መንገድ ቅን ነውና፤ ጻድቃን ይሄዱበታል፤ ዓመጸኞች ግን ይሰናከሉበታል።" ሆሴ 14፡8-9

1. ሆሴዕ 13፡1-14፡9 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3 ላይ ያለውን ክፍል ስናነብ፤ በቁ1 ላይ ኤፍሬም አስቀድሞ የነበረበትን፣ ቀጥሎ በቁ2 ላይ ደግሞ ኤፍሬም አሁን የሚገኝበትንና፤ በመቀጠል ደግሞ በቁ3 ላይ የኤፍሬምን የወደፊቱን እጣ ክፍሉ ምን እንደሚሆን እግዚአብሄር በግልጽ አስፍሮታል። የኤፍሬም በተለያየ ደረጃ የነበረውን፣ ያለበትንና ወደፊት ይሆናል የተባላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ከክፍሉ እያወጣህ ተናገር።
2. ሆሴ 13፡4-6ትን ደግሞ ስንመለከት፤ እግዚአብሔር ለህዝቡ ያደረገውን ሲነግረን፤ በአንጻሩ ደግሞ እርሱ ሕዝቡ ያገኘውን ምላሽ ይነግረናል። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስታይ፤ እግዚአብሄር ለህዝቡ አደረግሁላቸው በማለት የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? በቁ6 ላይ ደግሞ የምንመለከተው እግዚአብሄር ለህዝቡ ላደረገላቸው ነገር የሰጡትን ምላሽ በተዋረድ ያስቀመጣቸውን ሶስቱን ሃሳቦች ተናገር። እግዚአብሄር በህይወትህ ለሚያደርግልህ በጎ ነገር ምላሽህ ምን ይሆን?
3. በቁ9 ላይ እስራኤል ካደረጋቸው ክፉ ነገሮች መሃል ለጥፋቱ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን እግዚአብሄር ይናገራል፤ እነዚህ ለእስራኤል ጥፋት ምክንያት የሆኑት በዚህ ክፍል የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በቁ10 እና 11 ላይ እግዚአብሄር ንጉስ በማለት የሚነገርለት ሰው ማን ነው ብለህ ታምናለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክም አስረዳ።
4. የኤፍሬም ሃጥያት እንደበዛ፣ እግዚአብሄር ደግሞ ሃጥያቱን ሁሉ መዝግቦ እንደያዘ፣ ስለዚህም ጽዋ እንደሞላ ከቁ12 ላይ እንረዳለን። ቁ13 ላይ ግን እግዚአብሄር አዲስ ጅማሬ ሊሰጠው እንደፈለገ የሚነግረን ምንን በመጠቀም ነው? ምንም እንኳን እግዚአብሄር ከቸርነቱ ብዛት የተነሳ ይህንን የማይገኝ ዓይነት ቢሰጠውም እንኳን፤ ኤፍሬም ይህንን የእግዚአብሄር ሥጦታ ያስተናገደበት መንገድ ምን ይመስላል? አንተስ እግዚአብሄር አዲስ ጅማሬን ሊሰጥህ የሚያመቻችልህን ሁኔታ ምን ያህል ትጠቀምበታለህ?
5. ሆሴ 14፡1-2 ላይ እግዚአብሄር አምላክ በነብዩ ሆሴዕ ውስጥ ሆኖ ለእስራኤል ህዝብ የሚመከረውን ምክር በማንበብ፤ አንድ ቃል ብቻ በመጠቀም ሃሳቡን ግለጥ ብትባል ምን ትላለህ? ከቁ1-3 ውስጥ ያለውን ክፍል ስናነብ፤ እግዚአብሄር ራሱ እንዴት ብለው እግዚአብሄርን መለመንና ንስሃቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ ቃላትን በአፋቸው ውስጥ ሲያኖር እንመለከታለን። እግዚአብሄር በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለንስሃ ሲቀርቡ ምን ብለው እንዲናገሩ ነው የሚመክራቸው?
6. እስራኤል እግዚአብሄር በነገራቸው መልኩ ከልባቸው ወደ እርሱ ከተመለሱ እንደሚሆንላቸውና እንደሚያደርግላቸው ከቁ4 ጀምሮ እስከ ቁ7 ባለው ክፍል ውስጥ ቃል የገባላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። በቁ4 ላይ እግዚአብሄር ህዝቡን "እንዲሁ እወዳቸዋለሁ" በማለት ሲናገር እንመለከተዋለን፤ ይህንን ማለቱ ምን ማለቱ እንደሆነ ነው የምትረዳው? እግዚአብሄር በዚህ ሥፍራ ላይ ለእስራኤል የተናገረው እውነት ለእኛም ለአዲስ ኪዳን አማኞች እውነት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል።
7. ቁ8 ላይ ስናነብ እስራኤል በንስሃ ተመልሶ በቁ4-7 ላይ ያለውን ዓይነት ሕይወት መኖር ሲጀምር፤ በእግዚአብሄርና በእርሱ መካከል ያለው የግንኙነት ዓይነት ደግሞ እንደዚሁ እንደሚቀየር ግልጽ በማድረግ ይነግረናል። በቁ8 ላይ በምናየው መሰረት የእግዚአብሄርና የእስራኤልን ግንኙነት የሚገልጹትን ቢያንስ አራት ነገሮች ተናገር።
8. ቁ9 መሰረት ጥበበኛ የሆነ ሰው እንደ ሚያስተውለውና፤ አስተዋይ የሆነ ሰው እንደሚረዳው የተነገረው ነገር ምንድነው? ይህ ቁጥር ጻድቃን ይሰሙታል፤ ወይም ይማሩታል ሳይሆን የሚለው፤ ጻድቃን ምን ያደርጉታል ነው የሚለን? አንተስ እውነትና ቅን የሆነውን የእግዚአብሄር መንገድ ትሰብከዋለህ፣ ታስተምረዋለህ ወይስ ደግሞ ትሄድበታለህ? የእግዚአብሄር መንገድ የምንሄድበት ወይም የምንመላለስበት ነገር እንጂ፤ እንዲሁ በከንቱ የምንሰማው፣ ወይም ለሌሎች የምናሰማው ብቻ ሊሆን አይገባም።